*ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ*

**Coalition for Unity and Democracy Party (Kinijit)**

***http://www.kinijitethiopia.org***

e-mail kil@kinijitinternational.org Voice Mail/Fax 1-206-203-3974

ጋዜጣዊ መግለጫ

ኪ.ል-013/07
ሚያዝያ 25 ቀን፣ 1999ዓ.ም

# ህዝባዊ ዕምቢተኝነት የሰላማዊ ትግሉ የማዕዘን ድንጋይ ነው !!

ወያኔ/ኢህአዴግ የሚሊኒየሙን በዐል በማስታከክ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁስሎችን ሳያሽር ሽፋፍኖ የኢትዮጵያን ገፅታ ለዐለም ለማስተዋወቅ በሚል መርህ ስር ሚሊኒየሙ በታሪካዊ፤ ባህላዊና፤ ማህበራዊ ሂደቶች ላይ ብቻ ያተኮረ ሆኖ ፖለቲካዊ የጥሪ አላማ እንዳይኖረው በመራወጥ ላይ ይገኛል። ከሁሉም በላይ ግዛቱ ሰላምና መረጋጋት የሰፈነበት ነው፣ ባገርም ውስጥ ይሁን በውጭ የሚገኘው ኢትዮጵያዊ ደጋፊየ ነው፣ ስጠራው ይመጣል ስዘፍን ያጨበጭባል፣ ፍትህን አዛባህ፣ የተቃዋሚ መሪዎችን አሰርክ ብሎ ቅሬታም አልተሰማውም የሚል የፖለቲካ ትርፍ ለመሸመት ተዘጋጅቷል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ደግሞ አምቆ የያዘው ስሜቱ፦

*“ለዘመናት በመረረ ድህነትና ጭቆና ስሰቃይ ኖሬ በታሪኬ ለመጀመሪያ ግዜ መሪዎቼን በድምጼ በመምረጥ፤ በሰላም በፍቅርና በአንድነት ጎዳና ላይ ዲሞክራሲን ምርኩዜ አድርጌ ጉዞ ልጀምርበት የነበረውን የተስፋ ጭላንጭል በአምባገነንነት ጋርደህብኛል።*

*ለእኔ መብትና ነጻነት ለአገርም ፍቅር ሲሉ፣ የሰጠሁዋቸውን አደራ ጠብቀው፤እምነታቸውን ሳይክዱ፣ ማተባቸውን ሳያላሉ ውድ መሪዎቼን ከአረጋዊ እስከ ወጣት፤ ከእናት እስከ አያት፤ ከምሁር እስከ ጨዋ፤ ከህብታም እስከ ድሀ በወህኒ አጉረኀብኛል።*

*ለድምጼ መከበር በአደባባይ የቆሙልኝን ረሽነህብኛል ፤ለእውነትና ለነጻነት የቆሙ ልጆቼን ኑሮአቸውንና ቤተሰባቸውን ትተው እንዲሰደዱ አድርገህብኛል።*

*ይባስም ብለህ በለኮስከው የጎሳ ፖለቲካ እየተለበለብኩ፤ ዕድሜህን ለማራዘም እየቆሰቆስከው ባለው የሀይማኖት ልዩነት እሳት ልትማግደኝ ድምበር ጥሰህ ጦር ሰብቀህ ወንድሞቸንና እህቶቸን በግዴታ አዝምተህ እያስለበለብክብኝ ነው።*

*በስሜ፣ ታሪኬና ባህሌን ለማስተዋወቅ በሚል ካባ ተጀቡነህ የጭቆናን ምዕተ አለም በጭቆና አገባደህ አዲሱን ምዕተ አለም በጭቆና አታስጀምረኝም።”* በማለት ወያኔን በተገኘው አጋጣሚ እየታገለና እየተጋፋጠ ይገኛል።

**ውድ ኢትዮጵያውያን**

ሕዝባችን ሠርቶ መብላት፤ወልዶ ማሳደግ፤ተምሮ ስራ መያዝ፤ታሞ መታከም አቅቶት በድህነት ማጥ ውስጥ እስከ አንገቱ ተነክሮ ይሰቃያል። ብዙሀኑ ኢትዮጵያዊ አዳዲስ ልብስ ገዝቶ፤በግና ዶሮ አርዶ፤የቅርጫ ስጋ አስገብቶ፤ጠላና ጠጅ ጠምቆ፤ጠርሙስ ውስኪ ከፍቶ፤ምሽቱን ወደ ሙዚቃ ቤቶች ሄዶ አሼሼ ገዳሜ በማለት ለማክበር አቅም ያለው አይደለም። ኢህአዴግ ”የጠገበ፣ የተራበ ያለ አይመስለውም” እንዲሉ በስጋዊ ድህነትና በመንፈሳዊ ባርነት ኮድኩዶ የያዘውን ሕዝብ ለኔ ጥጋብና ድሎት ና ጓይላ ጨፍር በማለት ላይ ይገኛል።

በውጭ ያለውን ኢትዮጵያዊ ደግሞ በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ መድቦ ከኢትዮጵያ ህዝብ ደጀንነቱ ለማዘናጋት፤ እርስ ብርሱ ለማጋጨት፤ በጥቅም ለመከፋፈል ደባውን ሸርቧል። በገዛ አገሩ እስረኛ ለሆነው ወገኑ አለኝታነቱን ለማዘናጋት፤ የህግ የበላይነትን ፤የተቃዋሚ ድርጅቶች መሪዎች መፈታትን ጥያቄ በታፈነው ህዝብ ስም እንዳያስተጋባ በጥቅም ለመደለል ሸር ጉድ ይላል። የሚላንየሙን ዝግጅት ተገን በማድረግ የፖለቲካ ጥያቄዎችን ወደጎን የሚያደርግና በተለይ በውጭ የሚኖረውን በጥቅም ለመደለል እየተካሄደ ያለው ርብርብ የኢትዮጵያን ህዝብ ስቃይና ሰቆቃ የሚያዘናጋ መሆኑን ወገኖች እንዲገነዘቡት እንወዳለን።



**Kinijit International Political Leadership Secretariat, P.O.Box 14701 Silver Spring MD, 20911 USA**
**Fax / Voice Mail. +1-206-203-3974 www.kinijitethiopia.org**

ሚላንየሙን ልናከብረው ይገባል። በኢኮኖሚ፣ በትምህርት፣ በጤና፣ በባህልና በማህበራዊ ኑሮ የደረስንበትን ደረጃ ልንቃኝም ይገባናል። ከሁሉም በላይ ግን የፖለቲካ ተስፋችን፣ የዲሞክራሲ ረሃባችን፣ የህግ የበላይነት ጥያቂያችን የታሰሩ መሪዎቻችን ነጻነት፣ የሚላንየም ዝግጅታችን እምብርት ሊሆን ይገባዋል። ይህን መሰረታዊ የህዝብ ጥያቄ ማእከል ያላደረገ ዝግጅት የወያኔ/ኢህአዴግን የማዘናጋት ሴራ ከማጀብ ውጭ ለለውጥ ፈላጊው የኢትዮጵያ ህዝብ ምንም እርባና አይኖርውም።

የኢትዮጵያን ህዝብ የፖለቲካ ነጻነት፣ የዲሞክራሲ ተስፋ፣ የመሪዎቻችንን መፈታት ለማረጋገጥ፣ ብሎም ለዚህ የህዝብ ፍላጎት ኢሃዴግን ተገዥ ለማድረግ፣ ሁለት አማራጮች ሊቀርቡ ይችላሉ። አንዱ ኢህአዴግን በሚያውቀው ቋንቋ በሃይልና በጉልበት ማንበርከክ ሲሆን፣ ምንም እንኳን ህዝባችንን ወደዚህ አቅጣጫ ቢገፋፋውም በዘላቂነት አይጠቅመኝም ብሎ በማመኑ በትእግስት ይህን መንገድ አልመረጠውም። የሚቀረው አማራጭ ስላማዊ ህዝባዊ ትግልን በ “ህዝባዊ እምቢተኝንት” በማጀብ ኢህአዴግን በማይገባው ቋንቋ ማስጨነቅ መቀጠል ነው። ስለሆነም በሽዎች የሚቆጠር የኢትዮጵያ ህዝብ በጥቅል፣ መሪዎቻችን ደግሞ በተናጠል መብትና ነጻነትን ለማስከበር ባላቸው ቁርጠኝነት በተገደሉበት፤ በታሰሩበት፤ በተሰደዱበት መስዋዕትነት አንጻር ሲመዘን ኢምንት የሆነ የትግል ድርሻ ባገር ውስጥም በውጭም ሃገር ካለነው ለውጥ ፈላጊ ኢትዮጵያውያን ይጠበቅብናል።

ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ በዚህ ጉዳይ ያለውን ሁኔታ ከመረመረ በሗላ የሚከተለውን ጥሪ ለህዝባችን ያቀርባል።

ወያኔ/ኢሃዴግ ለዴሞክራሲ፣ ለህዝብ ድምጽ መከበር፣ለህግ የበላይነት፣ ባጠቃላይ ለህዝብ ፍላጎት በመቆማቸው ምክንያት፣ በሃሰት ወንጅሎ፤ በእስር የሚያማቅቃችውን የቅንጅት መሪዎች፣ አባላትና ደጋፊዎች፣ በሰበብ አስባቡ በወህኒ ያጎራቸውን የህሊና እስረኞች፤ **ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ከእስር እንዲፈታ እንጠይቃለን። ይህን ለመፈጸም ፈቃደኛ ካልሆነ፣** ቀጣይነት ያለው ሁሉን አቀፍ ህዝባዊ ተቃውሞና እምቢተኝነት ጥሪዎችን በአገር ውስጥም ይሁን በውጭ ያለ ኢትዮጵያዊ ሁሉ እንዲሳተፍ፣ ጥሪ እናቀርባለን።

1. *በሃገርም ውስጥ ሆነ በውጭ ሃገር የሚደረግ የሚላንየም አከባበር ኢሃዴግና አቀንቃኞቹ እንደሚመኙት፣ ባህላዊና ማህበራዊ ይዘት ብቻ ኖሮት የሃሴትና የፈንጠዝያ ወቅት ሳይሆን፤ ያለፈው ሚላንየም፣ ወያኔ/ኢሃዴግ ያገራችንን የዴሞክራሲ ተስፋ ያመከነበት፤ የፖለቲካ ነጻነት ውጋገንን ያዳፈነበት መሆኑን በመገንዘብ፣ በምሬትና በብሶት ትግሉን የማፋፋም ስሜቱን የሚያጠናክርበትና ህዝባዊ ቁጣውን የሚያገነፍልበት ወቅት ሊያደርገው ይገባል።*
2. *ማንኛውም ኢትዮጲያዊ ሊሰረዝ የማይችል ግላዊና ቤተሰባዊ ችግር ካልገጠመው በስተቀር ሚሊኒየሙን ለማክበር ብቻ ወደ አገር ቤት ለመሄድ ያለውን እቅድ እንዲመረምር፤ ከሄደም ራሱን ከብአሉ አከባበር እንዲያገል። በዚህም የኢኮኖሚና የስሜት መስዋእትነት በመክፈል ወያኔ/ኢሃዴግ በእስር የሚያሰቃያቸውን የህሊና እስረኞች እንዲፈታ ጫና በመፍጠር አስተዋጻኦ እንዲያደርግ።*
3. *በዜግነታችን ልናገኝ የሚገባንን ጥቅም በችሮታ የሰጠ ለመምሰል የሚያደርገዉን መመጻደቅ በህዝባዊ እምቢተኝነት የጥቅም ሳይሆን የህዝብ ወገንተኝነታችንን ማሳየት ተገቢ ነው።*
4. *በየአካባቢው የሚከበረው የሚሊኒየሙ በአል የኢትዮጵያ አኩሪ ታሪካዊና ባህላዊ ዕሴቶች የሚንጸባረቁበት ብቻ ሳይሆን፣ ሕዝባችን ከምዕተ አለሙ ጭቆና ተላቆ አዲሱን ምዕተ አለም በአዲስ ምዕራፍ እንዲጀምር የሚያስችል ፖለቲካዊ የትግልና ህዝባዊ እንቢተኝነት ጥሪ መርሁ ያደረገ የተጠናከረ ህዝባዊ ትግል የሚፋፋምበት በማድረግ የሃገርን አደራ እንድንወጣ ቃል ኪዳናችንን ልናድስ ይገባል።*

ድል፣ ህዝብ ለነጻነቱና ለመብቱ ካለው ጥማት በሚመነጭ ቁርጠኛነቱ በዕምቢተኝነት ከጨቋኝ አገዛዝ እጅ ፈልቅቆ የሚያወጣው ክስተት ነው። ሁላችንም ኢትዮጵያውያን ከህዝባችን ጋር ያለንን የትግል አጋርነት ለመግለጽ የወያኔን የሚሊኒየም ‹ኑልኝ› ጥሪ በማክሸፍ የሰላማዊ ትግሉ የማዕዘን ድንጋይ በሆነው ህዝባዊ ዕምቢተኛነት ስር መሰባሰብ የወቅቱ የትግል ድርሻችን ሊሆን ይገባዋል።

የሚሊኒየሙ በአል የኢትዮጲያ ህዝብ ከዘመናት ጭቆና ለመላቀቅ የትግል ስሜቱን የሚያጠናክርበት መድረክ ነው !!!

**ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ**
**አለም አቀፍ የፖለቲካ ኮሚቴ**



**Kinijit International Political Leadership Secretariat, P.O.Box 14701 Silver Spring MD, 20911 USA**
**Fax / Voice Mail. +1-206-203-3974 www.kinijitethiopia.org**